ነጻ የጥርስ፣ የእይታ እና የህክምና እንክብካቤ

SEATTLE/KING COUNTY CLINIC

ኤፕሪል 29 – ሜይ 2፣ 2027 በ Seattle Center



ስለ ክሊኒኩ

- **በየቀኑ ውሰን የመግቢያ ትኬቶች ብዛት ይገኛሉ፣** ጠዋት 5:30 በSeattle Center (200 Thomas St) በሚገኘው Fisher Pavilion ይሰራጫሉ።
- የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች በሙሉ ወይም በዚያው ቀን የሚቀርቡ አገልግሎቶችን ማግኘት ላይችሉ ይችላሉ የጥርስ እና የዓይን ህክምናን በዚያው አንድ ቀን ውስጥ አያገኙም።
- ቀጠሮ ወይም ቅድመ ምዝገባ የለም - **መጀመሪያ የመጣ፣ መጀመሪያ ይስተናገዳል**
- የህመምስሜትካለዎትአይሳተፉ
- አስተርጓሚዎችአሉ
- በMercer St. Garage (650 3rd Ave N) ነጻየመኪና ማቆሚያ
- **ምግብ፣ የሚመች ልብስ እና የሚወሰዱ መድሀኒቶችን ይዘው ረዘም ላለ ጊዜ ለመቆየት ተዘጋጅተው ይምጡ**

ሁሉም አገልግሎቶች ነጻ ናቸው

የጥርስ፦ የህመም ወይም የምቾት ማጣት፣ የታወቁ ወይም የተጠረጠሩ የተቦረቦሩ ጥርሶች፣ የድድ እብጠት፣ የተሰበረ ጥርስ ህክምና።

እይታ:- የእይታ ምርመራ፣ የተሟሉ የአይን ምርመራዎች፣ በሐኪም የታዘዘ የዓይን መነፅር። የዓይን ምርመራን ለመዝለል እና የዓይን መነፅር ለማግኘት ኦፊሴላዊ የታተመ የዓይን መነፅር ማዘዣ (ከሁለት ዓመት በታች) ይዘው ይምጡ።

ህክምና፦ የመጀምሪያ ደረጃ እንክብካቤ፣ የተመረጡ የላብራቶሪ ምርመራዎች፣ ማሞግራም፣ አልትራሳውንድ፣ ኤክስሬይ፣ ክትባቶች፣ የቆዳ ህክምና፣ የእግር እንክብካቤ፣ የአካል ህክምና፣ አኩፓንክቸር፣ የአመጋገብ ስርዓት፣ የባህሪ ጤና እና ሌሎችም።

ግብዓቶች፦ ማሕበራዊ ስራ፣ ከጤና መድህን ጋር እገዛ እና ተጨማሪ

ሁሉም እንቀበላለን!

- የጤና እንክብካቤ ለማግኘት እና/ወይም ከፍሎ ለመጠቀም ለተቸገረ ማንኛውም ሰው
- ታካሚዎች ምንም አይነት ID ወይም ሰነድ አያስፈልጋቸውም
- ታካሚዎች የሲያትል ወይም ኪንግ ካውንት ነዋሪዎች መሆን አያስፈልጋቸውም

ድረ-ገጽ፦
seattlecenter.org/patients
ኢሜይል፦
SKCClinic@seattlecenter.org
ስልክ፦
206.684.7200

ተጨማሪመረጃ፦

(ተጠናቋል)

ወደ ክሊኒኩ እንዴት መድረስ እችላለሁ?

- በ Seattle Center በሚገኘው Fisher Pavilion በመጣት ትኬት ይውሰዱ። ፊሸር ፓቪልዮን ዘወትር 12:30 AM ላይ ቀድመው ለሚደርሱ ታካሚዎች ክፍት ይሆናል (ለካርታ እና ዝርዝር መረጃ seattlecenter.org/patients ን ይመልከቱ)።
- ከመግባትዎ በፊት፣ ታካሚዎች እና እንግዶቻቸው የጤና ምርመራ ያደርጋሉ። ማንኛውም ፍሉ/ጉንፋን ወይም የኮቪድ አይነት ምልክቶች ያሉበት ሰው መግባት አይችልም።
- ዘወትር ከ 5:30 AM ጀምሮ ውስን ቁጥር ያላቸው ትኬቶች ይሰጣሉ። የሚሰጠው ትኬት ለዛ ቀን ብቻ የሚያገለግል ነው። ለአንድ ሰው አንድ ቲኬት።
- ታካሚዎች በትኬታቸው ላይ ባለው ቁጥር በቅደም ተከተል ወደ ክሊኒኩ ይገባሉ።

ለክሊኒኩ እንዴት መዘጋጅ አለብኝ?

- **ረጅም ቀን ሊሆን ይችላል። እራስዎን ለመጠበቅ ተዘጋጅተው ይምጡ።**
- ህመም የሚሰማዎት ከሆነ አይሳተፉ።
- ቀኑን ሙሉ የሚፈልጉትን ምግብ፣ ለስላሳ መጠጦች እና ማንኛውም መድሃኒቶች ይዘው ይምጡ።
- የቤተ ሙከራ ምርመራ ላይ እንዳይጾሙ።፡
- የጥርስ ህክምናን ለማግኘት፣ የደም ግፊትዎ እና የጉልኮስ መጠንዎ በተወሰነ ክልል ውስጥ ሊሆን
- ሞቹ ልብስ ይልበሱ።
- ሰለጠኑ አገልግሎት ሰጪ እንስሳቶች ካልሆኑ የቤት እንስሳቶች እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም።
- ዕድሜው ከ 18 ዓመት በታች የሆነውን ታካሚ ወላጅ ወይም ህጋዊ ሞግዚት አብሮት ሊመጣ ይገባል። ዕድሜያቸው 13 እና ከዛ በላይ የሆናቸው እና ወላጆቻቸው ወይም ህጋዊ ሞግዚቶቻቸው ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ልጆች ላይ ፈቃዶች ሊሰጡ ይችላሉ። እባክዎን ያስታውሱ፡ የህጻናት ስፔሻሊስቶች ለልጆች ህክምና ለመስጠት ላይገኙ ይችላሉ።

ሆነሰውቋንቋዬንየሚናገርይኖራል?

- በክሊኒኩ ሙሉ ትርጉም አለ

አንዴ ወደ ክሊኒኩ ከገባሁ ምን ይሆናል?

- ብዙ ቁጥር ያላቸው ታካሚዎች ይኖራሉ። **የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች በሙሉ ወይም በዚያው ቀን የሚቀርቡ አገልግሎቶችን ማግኘት ላይችሉ ይችላሉ** የጥርስ እና የዓይን ህክምናን በዚያው አንድ ቀን ውስጥ አያገኙም።
- ክሊኒክ ውስጥ ሲገቡ የይለፍ ካርድ ይሰጥዎታል። ይህ የይለፍ ካርድ የዚያን ቀን ብቻ ከክሊኒኩ ሕንጻዎች እንዲወጡ እና መልሰው እንዲገቡ ያስችልዎታል።
- ለክሊኒኩ ማለፍያ ይሰጥዎታል። ይህ ማለፍ ያለዚያች ቀን ከክሊኒኩ ህንጻዎች ለመወጣት እና ደግመው ለመግባት ያስችልዎታል።
- እንደ ስም፣ ዕድሜ እና የፖስታ መላኪያ አድራሻ ያሉ የላብራቶሪ ውጤቶችን እና የተጠናቀቁ የአይን መነጽሮችን ልንልክባቸው የምንችልባቸውን መሰረታዊ የግል መረጃዎችን እንሰበስባለን።
- በእያንዳንዱ የአገልግሎት መስጫ ቦታ (የጥርስ ህክምና፣ የአይን ወይም ሜዲካል) ወረፋዎ እስኪደርስ ይሰለፋሉ ከዚያም መጀመሪያ ለመጣት መጀመሪያ መስተንግዶ ይደረግለታል በሚለው መርህ መሰረት ይስተናገዳሉ (በዋናው ትኬትዎ ላይ ባለው ቁጥር ሳይሆን)።
- ለአገልግሎቱ በወረፋ ውስጥ ከሆኑ እና ቦታዎን ለረጅም ጊዜ ከተውት፣ በወረፋው ውስጥ ቦታዎን ያጣሉ እና በሚመለሱበት ጊዜ ወደ ወረፋው መጨረሻ ለመሄድ ያስፈልግዎታል።

Photos © Auston James

የማይሰጡ ምን ዓይነት አገልግሎቶች ናቸው?

የጥርስ ህክምና፦ የጎደሉ ጥርሶችን መግጠም፣ የመንጋጋ ጥርስን ጨምሮ ጥርስ ማውጣት፣ የሚወልቁ ሰው ሰራሽ ጥርሶች፣ በቀዶ ህክምና ጥርስ መትከል፣ ኦርቶዶንቲክስ፣ መንጋጋ ጥርስ ሙሌት፣ ማስታገሻ፣ የጥርስ እጥበትን ጨምሮ
ሜዲካል፦ ባዮፕሲ፣ ጀሶ፣ ሲቲ ስካን፣ ስፌት፣ ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት ክትባቶች፣ MRI፣ ለባህሪ ጤና መድሐኒቶች አዲስ ማዘዣዎች።
እይታ፦ በዓይን ላይ የሚለጠፍ ሌንስ፣ የጸሃይ መነጽሮች
ኦፒዮይድ ጥቅም ላይ አይውልም ወይም አይታዘዝም።

PARTNERS INCLUDE

AMN Healthcare · Arcora Foundation · Auston James Photography · Climate Pledge Arena
Dentsply Sirona · Ellison Foundation · Fred Hutchinson Cancer Center · Grousemont Foundation
Kaiser Permanente · Lucky Seven Foundation · OneSight EssilorLuxottica Foundation · Philips Healthcare
Project Access Northwest · Public Health-Seattle & King County · Quest Diagnostics · Seattle Center
Seattle Center Foundation · Seattle Information Technology · Snohomish County Dental Society
Underwood Gartland Development · UW School of Dentistry · Vitalogy Foundation
WA Healthcare Access Alliance · WA State Dental Association · WA State Department of Health